የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ—ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 12
ADDIS ABABA—17th January, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፮/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
ለቡታጅራ–ሆሳዕና–ሶዶ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ገጽ ፲፮፻፹፬

## CONTENTS

Proclamation No. 266/2002
African Development Fund Loan Agreement for Financing Butajira-Hossaina-Sodo Road Upgrading Project Ratification Proclamation ........... Page 1684

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፮/፲፱፻፺፬
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለቡታጅራ–ሆሳዕና–ሶዶ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ዩ.ኤ ፵፩ ሚሊዮን ፫፻፲ሺ (አርባ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ አሥር ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም ዓቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፱ ቀን፲፱፻፺፬ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለቡታጅራ–ሆሳዕና–ሶዶ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፮/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO. 266/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND*

*WHEREAS,* a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of UA 41,310,000 (forty-one million three hundred and ten thousand Units of Account) for financing the Butajira-Hossaina-Sodo Road Upgrading Project, was signed in Abidjan on the 16thday of November, 2001;

*WHEREAS,* basic economic international agreements have to be ratified prior to entry force;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 16thday of November, 2002.

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing Butajira-Hosaaina-Sodo Road Upgrading Project Ratification Proclamation No. 266/2002."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር 2100150006674 የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ.ኤ. ፵፩ ሚሊዮን ፫፻፲ሺ (አርባ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ አሥር ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement Number 2100150006674 signed in Abidjan on the 16[th] day of November 2001, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of UA 41,310,000 (forty-one million three hundred and ten thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 17[th] day of January, 2002.

Done at Addis Ababa, this 17[th] day of January, 2002

*GIRMA WOLDEGIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE